# ማሻሻል የተለመደ ሕግ ነው ።

## ከመምህር ኪዳነ ማርያም ገ፡ ሕይወት

የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ፩ኛ መጽሐፍ ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በነገሡ በ፴ኛው ዘመነ መንግሥት በ፲፱፻፶፪ ዓ. ም.

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የኢትዮጵያ ፓትሪያርክ በሆኑ በ፫ተኛው ዓመት ይህ መጽሐፍ በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አዲስ አበባ ነሐሴ ፫ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ. ም.

www.ethiopianorthodox.org

ቁጥር 5410

0911860113
Solomon Yohannes

# ማሻሻል የተለመደ ሕግ ነው።

## ከመምህር ኪዳነ ማርያም ገ፡ ሕይወት

የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ፩ኛ መጽሐፍ ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በነገሡ በ፴ኛው ዘመን መንግሥት በ፲፱፻፳፫ ዓ. ም.

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የኢትዮጵያ ፓትሪያርክ በሆኑ በ፫ተኛው ዓመት ይህ መጽሐፍ በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አዲስ አበባ ነሐሴ ፫ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ. ም.

www.ethiopianorthodox.org

ያለደራሲው ፈቃድ
ማሳተም በሕግ የተከለከለ ነው ።

# መግቢያ ።

## እናሻሽል ።

ማሻሻል የተለመደ ሕግ ነው ። ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀበት ምክንያት . . . . . የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጥንት ጀምሮ ከቅድስና ወደ ቅድስና ፤ ከዕውቀት ወደ ዕውቀት እየተራመደ የሚሔድ ዐዋቂ ሕዝብ ነውና ስለዚህ ጥንታዊውን የአባቶቻችንን የዕውቀት ቅርስ የሚገልጽ በዚህች ትንሽ መጽሐፍ የዕውቀትና የማሻሻል ሁኔታዎች በጥንቃቄ የተዘጋጁትን ለማወቅ እንድንችል ነው ።

፩ኛ· የኢትዮጵያ ሕዝብ በዛሬው ሥልጣኔ በሚያምር ሁኔታ አስፋፍቶ የያዘውን የሒሳብና የጆግራፊ ርምጃ እንደሌሎቹ የቅኝ አገሮች በሀገሩ ያልነበረውን ዕውቀት የተበደረ አይደለም ። የኢትዮጵያ ልጆች ዐዋቂዎች የዐዋቂዎች ልጆች ፤ ከዐዋቂዎች የተወለዱ መሠረታውያን ናቸው ። ይኸውም ስለሒሳብ አቈጣጠር በ፬ቱ መደቦች ማብዛት ፤ መቀነስ ፤ መደመር ፤ ማካፈል በኢትዮጵያ ከጥንት የነበረ መሆኑን በዚህ መጽሐፍ ለመረዳት እንችላለን ።

፪ኛ· ስለጆግራፊ ጥንታውያን አባቶቻችን ሲያስረዱ ጉዛውን ለፀሐይና ለጨረቃ ሰጥተው በ፲፱ ዓመት ፀሐይና ጨረቃ ዞረው በተፈጠሩበት በር ይገናኛሉ ሲሉ አስረድተዋል ። የዛሬው ትውልድ ደግሞ መሠረቱን ሳይለቅ ዕውቀቱን በማሻሻል አሳድጎ ፤ ጉዛውን ለመሬት ሰጥቶ መሬት ትዞራለች ይላል ።

ይህም የዕውቀት ማሻሻል ነው እንጂ አዲስ አይደለም ። ፀሐይና ጨረቃስ ዞረው የሚገናኙ መሆናቸውን

www.ethiopianorthodox.org

## መግቢያ ።

የሚያስረዳ ጥንታዊው የኢትዮጵያውያን አባቶቻችን
መጽሐፍ በሁሉም ዘንድ የታወቀ መሆኑን በዚሁ ጽሑፍ
ለመረዳት እንችላለን ።

፫ኛ. ስለበዓላትና ስለአጽዋማት በኢትዮጵያችን በ፬
ኛው ዘመን ጳጉሜን ፮ት በምትሆንበት ጊዜ በዓለ ልደት
ታኅሣሥ ፳፰ ቀን ስለሚከበር ከዚሁ ክብረ በዓል ቀጥ
ሎም በ፳፱ ቀን ረቡዕና ዓርብ ሲሆን በምእመናኑ ዘንድ
በየጊዜው ብዙ ችግር ይፈጥርባቸዋል ። ለሚጠይቁትም
ጥያቄ መልሱ በብዙ የተለያየ ድምፅ ስለሚያገኙ ፤ በየአ
ንዳንዳቸው ሳይግባቡ የሚኖሩ ወንድሞቻችን ብዙዎች
ናቸው ። ነገር ግን ማሻሻል ሁሉን የሚያስማማ ስለሆነ
በእኛ ዘመን ሳይሆን በጥንታውያኑ አባቶቻችን ሁኔ
ታው ተሻሽሎ የተወሰነው ጽሑፍ ተብራርቶ ባለመገ
ለጹ ወንድሞቻችን የተቸገሩበትን ሁሉ በአጭር ለማስረ
ዳት ወይም ለመረዳት እንድትችሉ ከጥንታውያኑ አባቶች
ያገኘሁትን ዕውቀት በዚህች መጽሐፍ አብራርቼ ለወን
ድሞቼ ሳቀርብ የአባቶቻችንን መሠረት ሳንለቅ ማሻሻል
እንዲኖርብን ከማሳሰብ ጋር ነው።

መምህር ኪዳነ ማርያም ገብረ ሕይወት ።

---

# ማሻሻል የተለመደ ሕግ ነው ።

## የአንደኛ ደረጃ ትምህርት አንደኛ መጽሐፍ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ዱ አምላክ
እግዚአብሔር እምቅድመ ዓለም እንደ ዛሬ በአንድነት
በሦስትነት ሳለ ዓለምን ልፍጠር ብሎ አሰበ አስቦም አል
ቀረም ፳፪ቱን ሥነ ፍጥረት ፈጠረ ፤ ዘፍ ምዕ ፩-ቍ ፩ ።
ሲፈጥርም ሰውና መላእክትን ስሙን ለመቀደስ ክብ
ሩን ለመውረስ ነው ፤ ኋያውን ግን ለምግበ ሥጋ
ለአንክሮ ፈጠረ ፤ ዘፍ፡ ምዕ ፪ ቍጥር ፩ ፤ እግዚአብሔር
የፈጠረውንስ ሰው ተናግሮ ባልፈጸመው ነበር፤ ነገር ግን
ብዙውን አንድ እያሉ በየወገን በየወገኑ ቢቈጥሩ ከእ
ሑድ እስከ ዓርብ ያዘጋጀው ሥነ ፍጥረት ፳፪ ይሆናል ።

ይህ ዓለም የተፈጠረበት ዕለት እሑድ ጥ ን ተ
ዕለት ይባላል አዝርዕት አትክልት ዕፀዋት የተፈጠሩበት
ዕለት ሠሉስ ጥንተ ቀመር ይባላል ፀሐይ ጨረቃ ከዋክ
ብት የተፈጠሩበት ዕለት ረቡዕ ጥንተ ዮን ይባላል ፤..
. ። ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ ልደተ ክርስቶስ የነ
በረው ዘመን ቢቆጠር ፭ሺህ ፭፻ ዘመን ነው ፤ ከልደተ ክርስ
ቶስ እስከ ዛሬ ድረስ ያለው ዘመን ቢቆጥሩት ሺህ ፱፻፶፯
ዓመት ሆነ ከልደተ ክርስቶስ በፊት የነበረው ዘመን ዓመተ
ፍዳ ዓመተ ኵነኔ ተባለ፡ ከልደተ ክርስቶስ ወዲህ ያለው
ዘመን ግን ዓመተ ሥጋዌ ዓመተ ምሕረት ተባለ በመላው
ዓመተ ዓለም ይባላል ዓለም በሚለው ዓመተ ምሕረት ሲ ል
ይገኛል ስለ ምን ቢሉ ሰው ኃጢአት ሠርቶ ንስሐ ቢገባ
ከፈጣሪው ምሕረት የሚያገኝበት ዘመን ስለሆነ ጊዮርጊስ

www.ethiopianorthodox.org

ወልደ ዓሚድ ዓመተ ዓለምን ዓመተ ምሕረት ብሎ ተር ጕሞታል ፤ በዕለተ ኅሪት ሰማዕኩከ ወበዕለተ መድኃኒት ረዳእኩከ እንዳለ ።

ለዚህም መስፈሪያ መቊጠሪያ ፯ አዕዋዳት አሉት ምንና ምን ቢሉ ዓውደ ዕለት ፤ ዐውደ ወርኅ፤ ዓውደ ዓመት፤ ዓውደ ዓበቅቴ፤ ዓውደ ፀሐይ፤ ዓውደ ማኅተም፤ ዓውደ ቀመር ናቸው ዓውደ ዕለት ከእሑድ እስከ ቅዳሜ ያሉት ፯ቱ ዕለታት ናቸው እነዚህም አውራኅን ለማስገኘት ሲመላለሱ ይኖራሉ ዓውደ ወርኅ በፀሐይ ዘወትር ፴ ቀን በጨረቃ ፩ ጊዜ ፳፱ ቀን ፩ ጊዜም ፴ ቀን ይሆናል ይህም ዓመታትን ለማስገኘት ሲመላለስ ይኖራል ፤ ዓውደ ዓመት በፀሐይ ፫፻፷፭ ዕለት በጨረቃ ፫፻፶፬ ዕለት ነው ጥያቄ ምነዋ በፀሐይ ፫፻፷፭ ዕለት ፲፭ ኬክሮስ ፯ ክልኢት አይደለም በጨረቃስ ፫፻፶፬ ዕለት ፳፪ት ኬክሮስ ፩ ክልኢት ፵፯ ሣልሲት ፶፪ ራብኢት ፵፰ ኃምሲት አይደለም? ቢሉም መልስ ወውስተ ውኁድ ንብል እንከ ኢልብ ወኢ ፩ደ እንዳለ ፰-፰ ክልሞላ ብሎ ነው እንጂ ትርፍ ቊጥርስ እንደተናገርሽው አለ ዕለታትን አዕ ዋድ አላቸው አውራኅን የሚያስገኙ ስለሆነ ፤ አውራኅን አእ ዋድ አላቸው ዓመታትን የሚያስገኙ ስለሆነ፥ ዓመታትን አዕ ዋድ አላቸው ቀመርን የሚያስገኙ ስለሆነ ነው ።

ከ፯ቱ አዕዋዳት ፫ቱ በዕለት ፤ ፬ቱ በዓመት ይቈጠ ራሉ በዕለት የሚቈጠሩት ዓውደ ዕለት ዓውደ ወርኅ ዓውደ ዓመት ናቸው ፥ ፬ቱ በዓመት የሚቈጠሩት ዓውደ ዓበቅቴ ፤ ዓውደ ፀሐይ ፡ ዓውደ ማኅተም ፤ ዓውደ ቀመር ናቸው ዓውደ ዓበቅቴ ፲፱ ዓመት ነው በዚህም ፀሐይና



ጨረቃ መንገዳቸውን ሲፈጽሙ በተፈጠሩበት ኆኅት ይገና ኙበታል ነቢየ አሪት ሙሴ መምህራነ ወንጌል ሐዋር ያት ሊቀ ጳጳሳት ድሜጥሮስ ከ፳ው ፩ድ ከ፵ው ፪ት ከ፹ው ፬ት ከመቶ ከ፻ው ፭ት ብላችሁ ቊጠሩ ማለታ ቸው ከዚህ የተነሣ ነው ጠንቅቁ ሓሳበ እንዳለ ዓውደ ፀሐይ ፳፰ ዓመት ነው በዚህም ዕለትና ወንጌላዊ ይገ ናኙበታል ዕለቱ ረቡዕ ወንጌላዊው ማቴዎስ ነው ፡ ዓውደ ማኅተም ፸፮ ዓመት ነው በዚህም ዓበቀቴና ወንጌላዊ ይገናኙበታል ዓበቅቴው ፲፰ ወንጌላዊው ዮሐ ንስ ነው ማኅተም አለው ዓበቅቴው ለአበቅቴ ፍጻሜ እንደሆነ ወንጌላዊውም ለወንጌላውያን ፍጻሜ ነውና ፡ ዓውደ ቀመር ፭፻፴፪ ዓመት ነው በዚህም ዓበቅቴ ዕለት ወንጌላዊ ይገኙበታል ዓበቅቴው ፲፰ ወንጌላዊው ዮሐ ንስ ዕለቱ ሰኑይ ነው ፤ ሠሉሱ ማቴዎስ የሚል ነውና ፤ ቀመ ርን ፫ት ስም ቢሰጡ ዓውደ ቀመር ዓቢይ ቀመር ፤ ዓውደ ማኅተም ማዕከላዊ ቀመር ፤ ዓውደ አበቅቴ ንኡስ ቀመር ፡ ይባላል ፥ የዓቢይ ቀመር አንቀጹ ፲፱ ቊጥር ፭፻፴፪ ዓመት ነው ፤ የማዕከላዊው ቀመር መደቡ (አንቀጹ) ፯ ቊጥሩ ፸፮ ዓመት ነው ፤ የንኡስ ቀመር አንቀጹ (መደቡ) ፫ት ቊጥሩ ፲፱ ዓመት ነው ፤ ማሳሰቢያ ፬ት ንኡስ ቀመር አንድ ማዕከላዊ ቀመር ይሆናል ፡ ፯ት ማዕከላዊ ቀመር አንድ ዓቢይ ቀመር ይሆናልና ፤ አስተውሉ ፡ ዓለም ከተ ፈጠረ ዘመን ከተቆጠረ በ፭ ሺህ ከ፭፻ ዘመን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን ለማዳን ከሰማየ ሰማያት ወርዶ በክርሠ ማርያም አደረ (ተጸነሰ) ቀኑም

www.ethiopianorthodox.org

በ፭ ሺህ ፭፻ ዓመተ ዓለም መጋቢት ፳፱ ቀን እሁድ ነው ፤ ይኸውም ወንጌላዊውን ለማወቅ ፭ቱን ሺህ ከ፭ ፻ው ዘመን ለ፬ቱ ወንጌላውያን ሲከፍሉት አንድ ሺህ ፫፻፸፭ አንድ ሺህ ፫፻፸፭ ዓመት ይደርሳቸዋል ወንጌላዊው ዮሐንስ መሆኑ በዚህ ይታወቃል ፩ድ ሲተርፍ ማቴዎስ ፪ት ሲተርፍ ማርቆስ ፫ት ሉቃስ ሲተከከል ዮሐንስ ነው ። ሲፀነስማ ወንጌላውያን የት ኑረዋል መቸስ ታውቀዋል ቢሉ መዋርስ አልነበሩም መታወቅም አልታወቁም ነገር ግን ለቅዱስ ድሜጥሮስ ምሥጢረ ሰማይ ወምድር ፹፩ መጻሕፍት ተገልጸለት ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ ትስብእት የነበረውን ዘመን ለ፬ቱ ወንጌላውያን ቢያከፍላቸው ክፍለ ዮሐንስ ሆኖ ተገኝቷልና ስለዚህ ወንጌላዊው ዮሐንስ አለ ፡ እንደዚሁም ጥንተዮቱን ለማግኘት ቀኑን ለማወቅ ዓመተ ወንጌላውያኑን በሱባኤ ይገድፈዋል የአንዱን ክፍል ሺህ ፫፻፸፪ቱን ዓመት በ፯ት በ፯ት ሱባኤ ገድፎ ፫ ይቀራል ። ፫ የዮሐንስ ። ፫ የማቴዎስ ። ፫ የማርቆስ ። ፫ የሉቃስ አሥራ ሁለት ፲፪ት ይሆናል ወንጌላውያን በዓመት ጳጉሜን በዕለት አንድ ናቸው ፤ ዓለም ከተፈጠረ እስከ ትስብእት ፯ናይቱ ጳጉሜን አንድ ሺህ ፫፻፸፭ ቀን ሁናለች ሺህ ፫፻፸፪ቱን በ፯ ሱባኤ ገድፎ ፫ት ይቀራል ፲፪ና ፫ት ፲፭ ይሆናል ከ፲፭ቱ ፯ት ቢገድፉ ፰ ይቀራል አሐደ አእትት ለዘመን እንዳለ አንዱን ቢያትቱ ፯ት ይቀራል በዘመነ ትስብእት ፯ት ጥንተዮን ይሆናል መስከረም ማክሰኞ ይብታል የመስከረም ሰኒታ ጥር ረቡዕ ይብታል የከቲት ዓርብ መጋቢት እሑድ ይብታል እሑድ እስከ እሑድ ፰ እሑድ እስከ እሑድ ፲፭ እሑድ እስከ እሑድ ፳፪ እሑድ እስከ እሑድ ፳፱ ጌታችን



ኢየሱስ ክርስቶስ በ፭ ሺህ ፭፻ ዓመተ ዓለም መጋቢት ፳፱ ቀን በከርሠ ማርያም አደረ (ማለት ተፀነሰ) ።

፪ና| ስለ ልደት በዓል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለም ከተፈጠረ በ፭ ሺህ ፭፻፩ ዘመን በቤተ ልሔም ተወለደ ይኸውም ወንጌላዊውን ለማወቅ ከ፬ት ይከፍለዋል ፡ ሺህ ከ፫፻፸፭ ሺህ ከ፫፻፸፭ ደርሶ ፩ ይተርፋል ወንጌላዊው ማቴዎስ መሆኑን በዚህ ይታወቃል።ጥንተዮቱን ለማውጣት ቀኑን ለመረዳት ዓመተ ወንጌላውያኑን በ፯ በ፯ ይገድፈዋል ከሺህ ፫፻፸፭ቱ ሺህ ፫፻፸፪ቱን በሱባዔ ቢገድፉ ፫ ይቀራል ። ፫ የማቴዎስ፡ ፫ የማርቆስ ፡ ፫ የሉቃስ ፡ ፫ የዮሐንስ፡ ፲፪ ይሆናል ፡ እንዳለፈው ፫ የጳጉሜን ፡ ፩ ተረፈ ዘመን ፬ ይሆናል ፤ ፬ና] ፲፪–፲፮ ይሆናል ፡ ፲፬ በ፪ት ሱባዔ ቢገድፉ ፪ ይቀራል ፤ አንዱን አትቶ ፩ ጥንተዮን ይሆናል ፤

ስለዚህ መስከረም ረቡዕ ይብታል መስከረም ረቡዕ ሲብት ታኅሣሥ ማክሰኞ ይብታል ፤ ማክሰኞ እስከ ማክሰኞ ፰ ማክሰኞ እስከ ማክሰኞ ፲፭ ማክሰኞ እስከ ማክሰኞ ፳፪ ማክሰኞ እስከ ማክሰኞ ፳፱ ቀን ይሆናል ታኅሣሥ በ፳፱ ቀን በዘመነ ማቴዎስ በዕለተ ሠሉስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተወለደ ከትስብእት እስከ ልደት ቢቆጥሩ ፪፻፸፭ ቀን ይሆናል ማለት ከመጋቢት ፳፱ ቀን እስከ ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ፱ ወር ከ፭ ቀን ነው ፡ ስለዚህ የልደት በዓል አቈጣጠር መነሻው መጋቢት ፳፱ ቀን መድረሻው ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ነው ፤ ከዚህ በላይ ትስብእት በዘመነ ዮሐንስ ልደት በዘመነ ማቴዎስ መሆኑን ተረድ

www.ethiopianorthodox.org

ተናል ፡ ነገር ግን ማሻሻል የተለመደ ሕግ ነው ፤ ያልንበትን ሁኔታ ከዚህ በጥቂቱ እንገልፃለን ፤ አባቶቻችን መነቃቀፍን አስወግደው በመግባባትና በመስማማት የልደትን በዓል በዓመት በዓመቱ ማክበር ስለፈለጉና ተገቢ ነገርም ስለሆነ በጥንቃቄ ሂሣቡን ሲያፋልሱ ማለት መዋዕለ ትስብእቱን ፪፻፸፰ ቀኖች በመጠበቅ ጳጒሜን ፮ በሆነ ጊዜ ፪፻፸፰ ቀኖች ታኅሣሥ ፳፰ ቀን ስለሚፈጸሙ በ፬ኛው ዘመን በዘመነ ዮሐንስ በዓለ ልደት ታኅሣሥ ፳፰ ቀን ይሁን ብለው አዘዋል ። ይህም ትእዛዝ የማሻሻል ሕግ ነው ፡ ምክንያቱም ቅዱስ ድሜጥሮስና በዘመኑ የነበሩ ሊቃውንት በዓላትና አጽዋማት የሚውሉባቸው ቀኖች ተገቢ ሥፍራቸውን እንዲይዙ አድርገው ወስነዋል ።

ይኸውም ፩ኛ ስለ፮ኛዪቱ ጳጒሜን ሁኔታ በሂሣብ አጣርተው ሲያስረዱ ፡ እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰማይንና ምድርን ፈጠረ የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል መሠረት አድርገው ሲነሱ ። ዘፍ. ም. ፩ ቁጥር ፩ እግዚአብሔር ይህን ዓለም በመጋቢት ፳፱ ቀን ፈጠረ ቀኑም እሁድ ነው ፡ እሁድ ፳፱ ሰኞ ፴ ቀን ይሆናል ጳጒሜን ማክሰኞ ይጀመራል ፡ ማክሰኞ ፩ ረቡዕ ፪ ሐሙስ ፫ ዓርብ ፬ ፡ ጳጒሜን አለቀ ፡ ጳጒሜን መሠረቱ ፬ ነው ፡ ሚያዝያ ቅዳሜ ይብቃል ፡ ግንቦት ሰኞ ይብቃል ፡ ሰኔ ረቡዕ ይብቃል ፡ ሐምሌ ዓርብ ይብቃል ፤ ነሐሴ እሁድ ይብቃል ፡ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ፫ ወር ከ፮ ቀኖች ቅዱስ ድሜጥሮስ በኬክሮስ ቈጥሮ በ፮ በ፮ ገድፎታል አንድ መዓልትና አንድ ሌሊት ፩፻፳ ኬክሮስ ይሆናል ።



ከመቶ ኻያው መቶ ፲፱ኙን ፩፻፲፱ በ፮ በ፮ ቢገድፉ አንድ ይተርፋል ፤ በዚሁ ሁኔታ የ፴ውን ቀንና ሌሊት ፴ ሠላሳ ኬክሮስ ይገኛል ፡ ኻያ ስምንቱን ኬክሮስ በ፬ አራት ሱባዔ ቢገድፉት ፪ ሁለት ይቀራል ማለት የአምስቱ ወር ፲ አሥር ኬክሮስ ይተርፋል ፡ ከ፮ቱ ዕለታትና ሌሊት ፮ ኬክሮስ ይተርፋል ፤ አንዱን አትቶ ፲፭ አሥራ አምስቱን ኬክሮስ ይዞ ዓመታትን መቍጠር ይጀምራል ፤ መስከረም ማክሰኞ ይብቃል በዚህ ሁኔታ ሠሉሱ ማቴዎስ ብሎ ዓመታትን ቀመረ ነገሩ እንዳይበዛ በሁለተኛው መጽሐፋችን አብራርተን እንገልፃለን።

፲፭ አሥራ አምስት ኪሮስ ብቻ ይዞ ዓመታትን በማቴዎስ ይጀምራል የማቴዎስ ፲፭ አሥራ አምስት ፡ የማርቆስ ፲፭ አሥራ አምስት ፤ የሉቃስ ፲፭ አሥራ አምስት ፤ ድምሩ ፵፭ ኪሮስ ይሆናል በአራተኛው ዓመት በዘመነ ሉቃስ ስድስተኛዪቱ ጳጒሜን ትገኛለች ሠገረ ዮሐንስ መባሏም እንዲህ ሁና በመገኘቷ ነው በዓላትና ዓውደ ዓመቶች ሁሉ በማቴዎስ ሰኞ የዋለ ፤ በማርቆስ ማክሰኞ ይውላል ቀጥሎም በሉቃስ ረቡዕ ይውላል ፤ በዮሐንስ ግን ሁልጊዜ በአራተኛው ዓመት ፮ ስድስተኛዪቱ ጳጒሜን ስለምትገኝ አንዱን ቀን ተራምዶ ዓርብ ይውላል ስለዚህ ሠገረ ዮሐንስ ተባለ ፮ ስድስተኛዪቱ ጳጒሜን በደረሰች ጊዜ የኢትዮጵያ፤ ምዕመናን ብዙ ሁከትና የመለያየት ስሜት ስለሚፈጠርበት ምክንያቱን ተረድቶ ማሻሻል አለበት ይህች ቀን በተገኘችበት ዘመን ሌሎቹን በዓላት ወደፊት በማሳለፍ ስትገፉ በዓለ ልደትን ወደ ኋላ ገትታ በ፳፰ቀን እንዲውል

www.ethiopianorthodox.org

ታደርገዋለች ምክንያቱም የልደት መነሻ መጋቢት ፳፱ ቀን ስለ ሆነ በዘመን መለወጫ እንደሚጀመሩ ሌሎቹ በዓላት ወደፊት ሊራመዱ አይችልም ሱባዔውን በመጠበቅ ከድሜጥሮስ በኋላ የተነሡትን ፫፻፲፰ ሊቃውንት አባቶቻችን ፪፻፸፭ ሁለት መቶ ሰባ አምስት ቀን የሚፈጸምበት በአራተኛው ዘመን ማለት በዘመነ ዮሐንስ ታኅሣሥ ፳፰ ቀን ነው ብለው በመወሰን ተስማምተውበት በዓለ ልደት ተብሎ ሲከበር እስከ ዘመናችን ደርሷል አሁንም ይህ በቍጥር ሁኔታ የተወሰነ ነገር የዘሬውም ሊቃውንት በበለጠ አስበውበት ሊሻሻል የሚችል ነው ስንል አሳባችንን ዘግተን ወደሌላው እንቀጥላለን ።

፫ኛ ስለ ጥምቀት በዓል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለም ከተፈጠረ በ፭ሺህ ከ፭፻፴፩ ዘመን በዮርዳኖስ ባሕር በእደ ዮሐንስ ተጠመቀ ይኸውም ወንጌላዊውን ለማወቅ ፭ሺህ ከ፭፻፴፩ ዘመን ከ፬ት ይከፍልዋል ፩ሺህ ፫፻፹፪ት ፩ሺህ ፫፻፹፪ት ደርሶ ፫ት ይቀራል ወንጌላዊው ሉቃስ መሆኑ በዚህ ይታወቃል ጥንተዮሩን ለማውጣት ቀኑን ለመረዳት ከሺህ ፫፻፹፪ቱ ሺህ ፫፻፸፱ኙን ነሥቶ በ፯ በ፯ት ገድፎ ፫ ይቀራል፤ ፫ት የሉቃስ፤ ፫ የዮሐንስ፤ ፫ የማቴዎስ፤ ፫ የማርቆስ፤ ፲፪ ይሆናል ፫ት የጳጉሜን፤ ፫ት ተረፈ ዘመን፤ ፮ት ይሆናል ፲፪ና ፮ት ፲፰ ይሆናል አሥራ አራቱ ፲፬ቱን በ፪ት ሰባዔ ገድፎ ፬ ይቀራል ፩ዱን አትቶ ፫ት ጥንተዮን ይሆናል መስከረም ዓርብ ይብታል የመስከረም ሳኒታ ጥር ቅዳሜ ይብታል ቅዳሜ እስከ ቅዳሜ ፰ እሁድ ፱ ሰኞ ፲ ማክሰኞ ፲፩ ቀን ይሆናል ከተወለደ በ፴ ዓመቱ ጥር



በ፲፩ ቀን ማክሰኞ ተጠመቀ ተጠምቆ ዕለቱን ገዳመ ቆሮንቶስ ገባ ያሉ እንደሆነ ከጥር ፳ ከየካቲት ፳፥፵ ይሆናል የካቲት ፳፩ ቀን ወጥቶ በ፳፫ ቀን በቃና ዘገሊላ ወኃውን ወይን አድርጓል አድሮ ገባ ያሉ እንደሆነ ከጥር ፲፱ ከየካቲት ፳፩፥፵ በየካቲት ፳፪ ቀን ወጥቶ በ፳፬ት ቀን ቃና ዘገሊላ ይሆናል፤ ሊቃውንት ግን የቃና ዘገሊላ በዓል የወኃ በዓል ከወኃ በዓል ይጥል ብለው ከጥምቀት ጋር ጥር ፲፪ ቀን እንዲውል ወስነው አምጥተው ጨምረውታል ይህም በማሻሻል ተስማምተው ስለወሰኑት ተለውጦ እስከ ዛሬ ድረስ ይሠራበታል ።

---

፬ኛ ስለ ደብረ ታቦር በዓል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለም ከተፈጠረ በ፭ሺህ ከ፭፻፴፫ ዘመን በደብረ ታቦር ብርሃን መለኮቱን ገለጠ ይኸውም ወንጌላዊውን ለማወቅ ከ፬ት ይከፍልዋል እንደ ሺህ ፫፻፹፫ት፤ ሺህ ፫፻፹፫ት ደርሶ ፩ ይቀራል ወንጌላዊው ማቴዎስ መሆኑ በዚህ ይታወቃል ጥንተዮሩን ለማውጣት ቀኑን ለመረዳት ከሺህ ፫፻፹፫ቱ ሺህ ፫፻፸፱ኙን ነሥቶ በ፯ በ፯ት ሱባኤ ገድፎ ፬ ይቀራል፤ የማቴዎስ ፬፤ የማርቆስ ፬ የሉቃስ ፬፥ የዮሐንስ ፬፥፲፮ ይሆናል፤ የጳጉሜን ፬ት ፩ ተረፈ ዘመን ፩፥ ፳፩ ይሆናል።

፲፬ቱን ሱባኤ ገድፎ ፯ ይቀራል ፩ዱን አትቶ ፮ት ጥንተዮን ይሆናል መስከረም ሰኞ ይብታል የመስከረም ሳኒታ ጥር ማክሰኞ ይብታል ጥር በባተበት ነሐሴ ማክሰኞ ይብታል ማክሰኞ እስከ ማክሰኞ ፰ት ረቡዕ ፱ ሐሙስ ፲ ዐርብ ፲፩ ቅዳሜ ፲፪ እሁድ ፲፫ ቀን ይሆናል በ፭ሺህ ፭፻፴፫ ዘመን ነሐሴ ፲፫ ቀን ቀኑ እሁድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደብረ ታቦር ብርሃን መለኮቱን ገለጠ ።

www.ethiopianorthodox.org

፳፭ ስለ ስቅለት በዓል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለም ፀተፈጠረ በ፭ሺህ ፭፻፴፬ ዘመን ተሰቀለ ይኸውም ወን ጌላዊውን ለማወቅ ከ፬ት ይከፍለዋል ከ፭ሺህ ፭፻፴፬ቱ ፭ሺህ ፭፻፴፪ቱን ነሥቶ ሺህ ፫፻፹፫ ሺህ ፫፻፹፫ ደርሶ ፪ት ይቀራል ወንጌላዊው ማርቆስ መሆኑ በዚህ ይታወ ቃል ጥንትዮኑን ለማውጣት ቀኑን ለመረዳት ከሺህ ፫፻፹ ፫ቱ ሺህ ፫፻፸፱ኙን ነሥቶ በ፯ት በ፯ት ሰብኤ ገድፎ ፬ት ይቀራል ፤ ፬ት የማርቆስ ፡ ፬ የሉቃስ ፡ ፬ የዮሐንስ ፡ ፬ ማቴ ዎስ ፡ ፲፮ ይሆናል ፡ የጳጉሜን ፬ት ፪ ፡ ተረፈ ዘመን ፯ ፡ ፲፮ትና ፯ት ፳፫ ይሆናል ፳፩ዱን በ፫ት ሰብኤ ገድፎ ፪ ይቀራል ፪ቱን አትቶ ፯ ጥንትዮን ይሆናል ፤ መስከረም ማክሰኞ ይብታል የመስከረም ሳኒታ ጥር ረቡዕ ይብታል የካቲት ዓርብ ይብታል መጋቢት እሁድ ይብታል እሁድ እስከ እሁድ ፲ እሁድ እስከ እሁድ ፲፯ እሁድ እስከ እሁድ ፳፬ እሁድ እስከ እሁድ ፴፩ እሁድና ቅዳሜን ቢቀንሱ ዓርብ ፳፯ ቀን ይሆናል ዓለም በተፈጠረ በ፭ሺህ ፭፻ ፴፬ ዘመን መጋቢት ፳፯ ዓርብ ቀን ጌታችን ኢየ ሱስ ክርስቶስ ተሰቀለ በዚሁ ቀን ሞተ ተቀበረ በ፫ኛውም ቀን ማለት መጋቢት ፳፱ ቀን በዕለተ እሁድ በአምላክነቱ ኃይል ተነሣ ዋናው በዓለ ትንሣኤ የሚውልበት ቀን መጋ ቢት ፳፱ ቀን መሆኑን በሁሉም ዘንድ የታወቀ ነው ነገር ግን ሊቃውንት በመስማማት አሻሽለው መሠረቱን ለቆ እስከ ሚያዝያ ፴ ቀን እየወጣ እስከ መጋቢት ፳፯ ቀን እየ ወረደ በ፴፭ ውስጥ በመዘዋወር በዓለ ትንሣኤ እንዲከበር



የተደረገው የሕዝቡን ሁኔታ በማየት ከእሁድ እንዳይወጣ ብለው ሊቃውንቱ ያሻሻሉት ነው ስለዚህ ማሻሻል የተለ መደ ሕግ ነውና ማንኛውም ነገር በጊዜው ሁኔታ እየታየ ሊሻሻል ይችላል ።

---

፳፯ ዓለም ከተፈጠረ እስከ ትስብእት የነበረውን ዘመን በዓቢይ ቀመር ፡ በማዕከላዊ ቀመር ፤ በንኡስ ቀመር ቢቈጥሩ ፲ ዓቢይ ቀመር ፪ ማዕከላዊ ቀመር ፤ ፩ ንኡስ ቀመር ሁኖ ፱ ዓመት ይተርፋል ፤ ይኸውም ተረፈ ዘመን ወይም ተረፈ ቀመር ይባላል ።

በንኡስ ቀመር ብቻ ቢቈጥሩ ፪፻፹፱ ንኡስ ቀመር ሆኖ ፱ ይተርፋል ፤ በማዕከላዊ ቀመር ብቻ ቢቈጥሩ ፳፪ ማዕከላዊ ቀመር ፤ ፩ ንኡስ ቀመር ሁኖ ፱ ዓመት ይተርፋል ፤ ፩ደ አእትት ለዘመን እንዲል ፤ ፩ዱን ቢያትቱ ፰ ይተርፋል ይኸውም ተረፈ ቀመር ይባላል ፤ መጥቅዑ ለማግኘት ከ፰ቱ ፲፱ ፤ ፲፱ ቢነሡ ፻፵፪ ይሆናል ። ፻፵ውን በ፴ በ፴ ሰብዔ ገድፎ ፪ ይተርፋል መጥቅዕ ማለት ይህ ነው ። አበቅቴውን ለማግኘት ከ፰ቱ ፲፩ ፲፩ ቢነሡ ፹፰ ይሆናል ። ፹ውን ገድፎ ፳፰ ይተርፋል ዓበቅቴ ማለት ይህ ነው ። እስከዚህ ያለው ሁሉ የማይለወጥ ጸንቶ የሚ ኖር አቈጣጠር ነው ።

---

፳፰ ስለ ፲፱፻፺፯ ዓ ም. በዓላትና አጽዋማት ። ዓለም ከተፈጠረ እስከ ዛሬ ድረስ ፯ሺህ ፬፻፺፯ ዘመን ሁኗል ስለዚህ ፯ሺህ ከ፬፻፺፯ ዘመን በዓቢይ ቀመር በማዕከላዊ ቀመር በንኡስ ቀመር ቢቈጥሩ ፤ ፩ኛ በዓቢይ ቀመር ብቻ ቢቈጥሩ ፲፬ ዓቢይ ቀመር ሆኖ ፰ ዓመት ይተርፋል ።

፪ኛ በማዕከላዊ ቀመር ብቻ ቢቆጥሩ ፸፪ ማዕከላዊ ቀመር ሆኖ ፳፰ ዓመት ይተርፋል ።

፫ኛ በንኡስ ቀመር ብቻ ቢቆጥሩ ፪፻፹፱ኙ ንኡስ ቀመር ሆኖ ፱ ዓመት ይተርፋል ።

ይኸውም ተረፈ ዘመን ይባላል ። ከ፱ኙ ፩ዱን አጕዶ ፰ ይተርፋል አሐዱ እኦተት ለዘመን እንዳለ መቍጠሪያችን ስለተጀመረ ማቴታችን ስላልተፈጸመ ነው ። የ፲፱፻፺፯ ዓ. ም. አበቅቴ ለማግኘት ከ፳፡ ተረፈ ዘመን ፲፩ ፲፩ድ ቢነው ፻፳፩ ይሆናል ። ፻ውን በ፬ ፴ ቢገድፉ ፲፩ አበቅቴ ይህ ናል የዘንድሮ አበቅቴ ይህ ነው ። መጥቅዕ ለማግኘት ከ፳፡ ፲፱ ፡ ፲፱ ቢነው ፩፻፺፩ ይሆናል ፩፻ ፹ውን በ፴ በ፴ ገድፎ ፲፱ መጥቅዕ ይሆናል የዘንድሮ መጥቅዕ ይህ ነው ፲፩ አበቅቴ ፲፱ መጥቅዕ ፴ ይሆናል ፡ አበቅቴ ቢበዛ መጥቅ ቢያንስ ከ፴ አይወጣም ከ፴ አይወርድም ዘወትር ፴ ነው ።

መስከረም ሐሙስ ይብታል ጥቅምት ቀዳሚ ይብታል ቀዳሚ እስከ ቀዳሚ ፹ ቀዳሚ እስከ ቀዳሚ ፲፭ ፪ ቢቀንሱ ሐሙስ ፲፫ ይሆናል በዓለ መጥቅዕ ጥቅምት ፲፫ ቀን ሐሙስ ይውላልየሐሙስ ተውሳክ ፫ ፲፫ና ፫ ፲፮ ይሆናል ነነዌ የካቲት ፲፮ ቀን ይውላል ዓቢይ ጾም የካቲት ፴ ቀን ይውላል ደብረ ዘይት መጋቢት ፳፮ ቀን ይውላል ሆሣዕና ሚያዝያ ፲፰ ቀን ይውላል፡ ስቅለት ሚያዝያ ፳፫ ቀን ይውላል፡ ትንሣኤ ሚያዝያ ፳፭ ቀን ይውላል ረክበ ካህናት ግንቦት ፲፱ ቀንይውላል፡ ዕርገት ሰኔ ፬ ቀን ይውላል ጰራቅሊጦስ ሰኔ ፲፬ ቀን ይውላል፡



ጾመ ሐዋርያት ሰኔ ፲፭ ቀን ጾመ ድኅነት ሰኔ ፲፮ ቀን ይውላል ። ፲፱፻፺፯ ዓ፡ ም፡ ውሳኔ ይኸ ነው ።

ቅዱስ ድሜጥሮስ የአዝማናትና የአጽዋማት ቍጥር በ፪፻፲፫ ዓ. ም. ጽፎታል ማለት ከሰርገት በኋላ በ፩፻፹ ዓመት ነው ።

---

ጥያቄ ይህ ዓለም የተፈጠረበት ቀን ምን ይባላል ?

መልስ እሁድ ፡

ጥያቄ በምን ወር በስንት ቀን እንደሆነ ወንጌላዊውም ማን እንደሆነ አስረዳኝ ?

መልስ ወሩ መጋቢት ቀኑ ፳፱ ቀንነው ወ ማቴዎስ ነው

ጥያቄ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ በክርሠ ማርያም ያደረበትን ዘመን አስረዳኝ ።

መልስ አ፭ ሺህ ፭፻ ዘመን ሲፈጸም ነው ።

ጥያቄ ወሩንና ቀኑን ለይተህ አስረዳኝ ?

መልስ መጋቢት ፳፱ ቀን እሁድ ነው ፡

ጥያቄ ወንጌላዊውስ ማን ነበር ?

መልስ ወንጌላዊ ዮሐንስ ነው ፡

ጥያቄ ሲዐነስማ ወንጌላውያን መች ነበሩ መችስ ታወቁ ?

መልስ መኖርስ አልነበሩም መታወቅም አልታወቁም ነገር ግን ለቅዱስ ድሜጥሮስ የአዝማናት ቍጥር በመንፈስ ቅዱስ ተገልጾለት ዓለም ከተፈጠረበት ጀምሮ ለ፬ቱ ወንጌላውያን ቢያከፍለው ክፍለ ዮሐንስ ሆኖ ተገኝቷልና ስለ ዚህ ወንጌላዊው ዮሐንስ ነው እንላለን ።

ጥያቄ በዚህ ዘመን የ፩ዱ ወንጌላዊ ክፍል ምን ያህል ነበር አስረዳኝ ?

www.ethiopianorthodox.org

መልስ የአንዱ ወንጌላዊ ክፍል ወይም ድርሻ አንድ ሺህ ፫፻፸፭ ዓመት ነው ፤

ጥያቄ ወንጌላዊው ዮሐንስ መሆኑ በምን ይታወቃል?

መልስ ክፍለ ዘመኑ ላ፬ቱ ወንጌላውያን ልክ ተስ ተካክሎ ሲደርሳቸው ዮሐንስ ነው ፩ ሲተርፍ ማቴዎስ ፪ ማርቆስ ፫ ሉቃስ ነው ፤

ጥያቄ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስንት ቀን በከርሠ ማርያም ኖረ ?

መልስ በከርሠ ማርያም የኖረው ፪፻፸፭ ቀን ወይም ፱ ወር ከ፭ ቀን ነው ፤

ጥያቄ ዓለም ከተፈጠረ በስንት ዘመን ተወለደ ?

መልስ በ፭ ሺህ ፭፻፩ (ዓ ም. ነው) ዘመን ነው ፤

ጥያቄ ወንጌላዊውና ወሩ እንዲሁም ቀኑን አስረዳኝ ?

መልስ ወንጌላዊው ማቴዎስ ወሩ ታኅሣሥ ቀኑ ፳፱ ቀን ማክሰኞ ነው ፤

ጥያቄ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በስንት ዓመት ተጠመቀ ?

መልስ በ፭ሺህ ፭፻፴፩ ዓ. ም. ነው የተጠመቀ ፤

ጥያቄ ወንጌላዊውና ወሩ እንዲሁም ቀኑን አስረዳኝ ?

መልስ ወንጌላዊው ሉቃስ ወሩ ጥር ቀኑ ፲፩ ማክሰኞ ነው ፤

ጥያቄ ፥ ከተወለደ በስንት ዓመቱ ተጠመቀ ?

መልስ ከተወለደ በ፴ ዓመቱ ነው የተጠመቀው ፤

ጥያቄ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተጠምቆ የት ሄደ ምንስ ሠራ ?



መልስ ተጠምቆ ገዳመ ቆሮንቶስ ገባ ። በዚያም ፵ ቀን ፵ ሌሊት ጾመ ፤

ጥያቄ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መዋዕለ ጾሙን ፵ ቀን ፈጽሞ የት ሄደ? ከሄደበት አገርስ ምን ሥራ ሠራ ?

መልስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መዋዕለ ጾሙን ፈጽሞ ወደ ገሊላ ሄዶ በአምላክነቱ ወኃውን ወደ ወይን ለወጠ ፤

ጥያቄ ወኃውን ወይን ያደረገበት ወርና ቀን አስረ ዳኝ ?

መልስ ወኃውን ወይን ያደረገበት የካቲት ፳፫ ቀን ማክሰኞ ነው ፤ ወይም ብለው የካቲት ፳፱ ቀን ነው የሚሉ አሉ ፤

ጥያቄ የቃና ዘገሊላ በዓል የካቲት ፳፫ ቀን ሲሆን በዓሉ የማይከበርበትን ምክንያት አስረዳኝ ?

መልስ የኋላ ሊቃውንት አሻሽለው የወኃ በዓል ከወኃ በዓል ይሁን ብለው ጥር ፲፪ ቀን ከጥምቀት ጋር ተያ ይዞ እንዲውል ስላዘዙ ነው ፤

ጥያቄ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለም ከተፈጠረ በስንት ዘመን ነው በደብረ ታቦር ብርሃን መለኮቱን የገለጸ ?

መልስ ብርሃን መለኮቱን የገለጸበት ዘመን በ፭ ሺህ ፭፴፫ ዘመን ነው ፤

ጥያቄ ወንጌላዊውና ወሩ እንዲሁም ቀኑን አስ ረዳኝ ?

መልስ ወንጌላዊው ማቴዎስ ቀኑ ነሐሴ ፲፫ ቀን እሁድ ነው ፤

www.ethiopianorthodox.org

ጥያቄ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለም ከተፈጠረ በስንት ዘመን ተሰቀለ ? በስንት ቀንስ ሙቶ ተነሣ ?

መልስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በ፭ሺ፭፻፴፬ ዘመን ተሰቀለ ሞተ። በሦስተኛው ቀንም ሙቶ ተነሣ።

ጥያቄ ወንጌላዊውንና ወሩን እንዲሁ ምቀኑን አስረዳኝ?

መልስ ወንጌላዊው ማርቆስ ወሩ መጋቢት ቀኑ ዐርብ ነው። ሦስተኛውም ቀን ሙቶ የተነሣበት እሁድ ነው ።

ጥያቄ የተሰቀለበትና የተነሣበትን ቀን መጋቢት ፳፯ና ፳፱ ቀን ከሆነ በዚሁ በተሰቀለበት በዓለ ስቅለት በተነሣበት በዓለ ትንሣኤ የማይከበርበትን ምክንያት አስረዳኝ ?

መልስ የኋላ ሊቃውንት ስቅለት ከዓርብ ትንሣኤ ከእሁድ እንዳይወጣ በማሰብ አሻሽለው በመስማማት ስለ ወሰኑ ነው ።

ጥያቄ ዓለም ከተፈጠረ እስከ ትስብእት የነበረውን ዘመን በዓቢይ ቀመር በማዕከላዊ ቀመር በንኡስ ቀመር ቢቈጥሩ ስንት ይሆናል ? ትርፉስ ምን ያህል ነው ።

መልስ አሥር ዓቢይ ቀመር ሁለት ማዕከላዊ ቀመር አንድ ንኡስ ቀመር ሆኖ ፱ ዓመት ይተርፋል ።

ጥያቄ ከዓቢይ ቀመር ከማዕከላዊ ቀመር ከንዑስ ቀመር የተረፈውን ፱ ዓመት ምን ይባላል ?

መልስ ተረፈ ዘመን ወይም ተረፈ ቀመር ይባላል ።

ጥያቄ በማዕከላዊ ቀመር ብቻ ቢቈጠር ስንት ማዕከላዊ ቀመር ይሆናል ስንትስ ይተርፋል ?

መልስ ፸፪ ማዕከላዊ ቀመር ሆኖ አንድ ንኡስ ቀመርና ፱ ዓመት ይተረፋል ።



ጥያቄ በንኡስ ቀመር ብቻ ቢቈጠር ስንት ንኡስ ቀመር ይሆናል ስንትስ ይተርፋል ?

መልስ ፪፻፹፱ ንኡስ ቀመር ሆኖ ፱ ዓመት ብቻ ይተርፋል ።

ጥያቄ ከንኡስ ቀመር የተረፈውን ፱ ዓመት ለምን ይጠቀማል ?

መልስ ፩ዱን አትቶ ፰ቱን መጥቅዕና ዓበቅቴን ያስገኛል ።

ጥያቄ አንዱን ቃትቶ ፰ቱን እንዲቈጠር የተደረገበት ምክንያት ምንድር ነው አስረዳኝ ?

መልስ የመጀመሪያው ዓመት ስለተጀመረ ተቈጠረ ስላልተፈጸመ ቃተተ ምክንያቱ ይህ ነው ።

ጥያቄ መጥቅዕና ዓበቅቴ ለማግኘት ከ፰ቱ ተረፈ ዘመን ስንት ስንት ቢነው ይገኛል ?

መልስ መጥቅዕ ለማግኘት ፲፱ ፲፱ ቢነው ። ዓበቅቴ ለማግኘት ፲፩ ፲፩ ቢነው ይገኛል ።

ጥያቄ መጥቅዕ ለማግኘት ፰ ጊዜ ፲፱ እንዲሁም ፰ ጊዜ ፲፩ ስንት ነው ?

መልስ ፲፱ ፲፱ኙ ፩፻፶፪ ፲፩ ፲፩ዱ ፹፰ ይሆናል ።

ጥያቄ ከ፩፻፶፪ና ከ፹፰ቱ መጥቅዕና ዓበቅቴ አውጥተህ አስረዳኝ ?

መልስ ከ፩፻፶፪ ፩፻፶ውን በ፴ በ፴ ቢገድፉ ፪ ይተርፋል ። መጥቅዕ ማለት ከ፴ው የተረፈ ፪ቱ ነው ። እንደዚሁም ከ፹፰ቱ ፷ውን በ፴ በ፴ ቢገድፉ ፳፰ ይተርፋል ። ዓበቅቴ ማለት ከ፴ው የተረፈ ፳፰ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

ጥያቄ ዓለም ከተፈጠረ እስከ ዛሬ ድረስ ማለት እስከ ፲፱፻፶፯ ዓ. ም. ስንት ዘመን ነው አስረዳኝ ?

መልስ ፯ሺህ፬፻፶፯ ዘመን ነው ።

ጥያቄ ይህንኑ በዓቢይ ቀመር በማዕከላዊ ቀመል በንኡስ ቀመር መድበህ ስንት ስንት እንደሆነ ለይተህ አስረዳኝ ?

መልስ ፩ኛ ፯ሺህ ከ፬፻፶፯ ዘመን በዓቢይ ቀመር ብቻ ቢቈጥሩ ፲፬ ዓቢይ ቀመር ሆኖ ፱ ዓመት ይተርፋል ፤ ፪ኛ በማዕከላዊ ቀመር ብቻ ቢቈጥሩ ፺፰ ማዕከላዊ ቀመር ሆኖ ፱ ዓመት ይተርፋል ። ፫ኛ በንኡስ ቀመር ብቻ ቢቈጥሩ ፫፻፺፪ ንኡስ ቀመር ሆኖ ፱ ዓመት ይተርፋል ። ዝርዝሩ ይህ ነው ።

ጥያቄ በየአንድ አንዱ ለ፩ የሚደርሰውን ድርሻ ለይተህ አስረዳኝ ?

መልስ ዓቢይ ቀመር ለ፩ዱ የሚደርሰው ፭፻፴፪ ዓመት ነው ። ማዕከላዊ ቀመር ለ፩ዱ የሚደርሰው ፸፮ ዓመት ነው ፤ ንኡስ ቀመር ለ፩ዱ የሚደርሰው ፲፱ ዓመት ነው ።

ጥያቄ የዘንድሮ ማለት የ፲፱፻፶፯ ዓ ም ዓበቅቴና መጥቅዕ አውጥተህ ስጠኝ ወይም አስረዳኝ ።

መልስ ዓበቅቴውን ለማግኘት ከ፱ቱ ተረፈ ዘመን ፩ዱን ቢያትቱ ፰ት ይተርፋል ከ፰ቱ ፲፩ ፲፩ድ ቢነሡ ፹፰ት ይሆናል ፹ን በ፴ በ፴ ቢገድፉ ፳፰ት ይቀራል የ፶፯ ዓ ም አበቅቴ ህይ ነው ፤ መጥቅዑን ለማግኘት ከ፰ቱ ፲፱፥፲፱ ቢነሡ ፩፻፶፪ ይሆናል ፩፻፶ውን በ፴ በ፴ ቢገድፉ ፪ት ይቀራል የዘንድሮ መጥቅዕ ይህ ነው ፤



ጥያቄ መጥቅዕ መሠረት ሆኖ ሲቆጠር ምንና ምን ያስገኛል ከምንስ ተጨምሮ ይቆጠራል አስረዳኝ ?

መልስ መጥቅዕ የዋለበትን ቀን ተውሳክ ዕለት ይዞ ነነዌን ብቻ በዚሁ ሲያስገኝ በዓላትንና አጽዋማትን በየአንድ አንዱ ተውሳኩን እያስጨመረ የሚውልበትን ቀን ዓመት እስከ ዓመት ያለውን ሁሉ ለይቶ ያስገኛል ።

ጥያቄ ዓበቅቴ መሠረት ሆኖ ሲቆጠር ምን ያስገኛል ? ከምንስ ተጨምሮ ይቆጠራል ፧

መልስ ዓበቅቴ ከሠርቀ መዓልትና ከሠርቀ ሌሊት ማለት ከመዓልትና ከሌሊት እየተቆጠረ በዕለቱ ያደረውን ሌሊት ያስረዳናል ፤ መልሱ መልካም ነው ።

በጥያቄው መሠረት መልሱን አጠናቅቆ እንዲያውቅ መምህር በተባለው ላይ እየጨመረ የበለጠውን ሁኔታ ቢያስረዳ አይከለከልም ፤ አንደኛው መጽሐፍ አበቃ ።

ተፈጸመ ።

ሁለተኛው መጽሐፍ ይቀጥላል ።

አስጀምሮ ላስፈጸመን አምላክ ክብር ምስጋና ይግባው ፤ ተከታዩንም ፈጽመን ወንድሞቻችን ሲጠቀሙበት ለማየት ያብቃን አሜን ።

www.ethiopianorthodox.org

፩ኛ የደብረ ሡልጣንና ጎልጎታ የኢትዮጵያ ገዳም አስረጂ
በኢየሩሳሌም በ፲፱፻፶ ዓ. ም.

፪ኛ ርትዕት ይእቲ ሃይማኖቶሙ ለቅዱሳን አበዊነ
በ፲፱፻፶፪ ዓ. ም.

፫ኛ ስለደብረ ሡልጣን የኢትዮጵያ ርስትነት
በ፲፱፻፶፫ ዓ. ም.

ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ
0911860113
0111/271609
D.N Solomon Yohannes

www.ethiopianorthodox.org